# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
# The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

## እምነት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ከሁሉም ቅድሚያ የሚሰጠው ሃይማኖት ነው ፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ ያለ ሃይማኖት እግዚአብሔርን ማገልገል እንደማይቻል ታምናለች። የእግዚአብሔር ን መንግሥት የሚወረሰው በሃይማኖት መሆኑን ለምእመናን ታስተምራለች።

## ህልዎተ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር መኖር)

እግዚአብሔር የሚለው የባሕርይ ስም ነው። ትርጉሙም ዓለምን ፈጥሮ የሚገዛ ማለት ነው። የማይታይና የማይመረመር ሁሉን ማድረግ የሚችል ሁሉንም የፈጠረ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ዘ ለዓለማዊ አምላክ መኖሩና ራሱን ለሰው ልጆች እንደገለጠ በቅዱሳት መጻሕፍት ተረጋግጧል። ዘጸአ.3፣6

የዚህን ዘለዓለማዊ አምላክ መኖር ከሚያስረዱን የአእምሮ ማስረጃዎች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

__ፍጥረት፤__ የሰው ልጅ አእምሮ የእግዚአብሔርን መኖር ለመረዳት ብዙ ተመራምሮአል። በምርምሩም የእግዚአብሔርን መኖር ወደማወቅ የሚያደርሱ መንገዶችን አግኝቶአል። ለማንኛውም ነገር ምክንያት አለው። ለሥእል ሠዓሊ፣ ለመጽሐፍ ጸሐፊ፣ ለወንበር ጠራቢ አለው። ለሚንቀሳቀስ ነገር ሁሉ አንቀሳቃ ሽ አለው። በዚህ መሠረት «ፍጥረት ያለ ፈጣሪ የተገኘ አይደለም» ወደሚለው እምነት ተደርሶአል። ፍጥረት ሁሉ ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ፤ አእምሮ ከሌለው ጀምሮ ከፍተኛ አእምሮ እስካለው ድረስ የእግዚአብሔርን መኖር ወደማወቅ ይመራል፤ ስለዚህም ሰሎሞን «እግዚአብሔርን የማወቅ ጉድለት በል ባቸው ያለባቸው ሰዎች ሁሉ በእውነት ከንቱ ናቸውና በእነዚህ በሚታዩ ፍጥረቶቹ በዚህ ዓለም የሚኖር እርሱን ያውቁ ዘንድ ተሳናቸው ሥራውንም እያዩ ፈጣሪያቸውን አላወቁም . . . ፀሐይና ጨረቃን አይተ ው የፈጠራቸውን ይወቁ . . .»(ጥበብ 13፤1-10) ይላል። ኢዮብም «እንስሶችን ጠይቅ ያስተምሩህማል። የሰማይ ወፎችን ጠይቅ ይነግሩህማል። ወይም ለምድር ተናገር ታስተምርሀለች፣ የባህርም ዓሣዎች ይነ ግሩሀል፣ የእግዚአብሔር እጅ ይህን እንዳደረገ ከእነዚህ ሁሉ ይህን የማያውቅ ማን ነው?» ብሏል (ኢ ዮብ 12፤ 7-9)። ቅዱስ ዳዊትም በመዝሙር 18፤ 1 -2 «ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፤ የሰ ማይ ጠፈርም የእጆቹን ሥራ ያወራል» በማለት ተናግሮአል።

ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስም ከዚህ ግልጥ በሆነ ሁኔታ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ለፍጥረቱ እንደሚ ታወቅ ሲያስረዳ እንዲህ ይላል። «ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ታይቶ የማይታወቅ እግዚአብሔር ለፍጥረቱ በሥነ ፍጥረት ይታወቃል።» (ሮሜ 1፤19-20)።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህን የሐዋርያውን መልእክት በተረጐመበት ድርሳኑ እንዲህ ይላል «እግዚአብ ሔር ገናናነቱ በሥራው ይታወቅ ዘንድ ሁሉን ካለመኖር ወደ መኖር አመጣ። ነፍስ በሰው ውስጥ እንደ ማትታይ ግን በሰውነት እንቅስቃሴ እንደምትታወቅ እግዚአብሔርም በሥጋዊ ዐይን አይታይም ግን በፈ ቃዱና በሥራው ይገለጣል ይታወቃልም። በባሕር ላይ ተንሳፍፋ ወደፊት የምትጓዝ መርከብን የሚመለከ ት ሰው በውስጥዋ የሚመራት ነጂ እንዳለ ማወቅ አለበት እንደዚሁም ምንም በዓይነ ሥጋ ባይታይ ሁሉ ንም የሚመራ እግዚአብሔር እንደሆነ ማስተዋል ይገባዋል።(የዮሐንስ አፈወርቅ ትርጓሜ፤ ሮሜ 1፤19-20)

__ልቡና፤__ «ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እን ኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና እነርሱም ልቡናቸው ሲመሰክርላቸው አሳባቸው እርስ በርሱ ሲካሰስ ወይም

ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ።» (ሮሜ 2፤14 - 15)። ሰው በልቡናው ውስጥ ባለው መንፈሳዊ ሕግ አነሳሽነት መልካም ይሠራል ከክፉም ይርቃል። ተላልፎ ክፉ ቢሠራም እንኳ ሕሊናው ይወቅሰዋል። መልካም የሚሠራ ዋጋ እንደሚያገኝ ክፉ የሚሠራም እንደሚቀጣ ይኸው ሕሊናው ይመሰክርበታል። ይህ ዓይነቱ ሕሊና ለደግም ሆነ ለክፉ እንደ ሥራው ዋጋ የሚከፍል አንድ አምላክ መኖሩን ወደ ማወቅ ይመራል።

<u>ታሪክ፤</u> በዚህ ዓለም አምልኮት የሌለው ሕዝብ እንዳልኖረ የሰው ልጅ ታሪክ ያስረዳል። ከጥንት ጀምሮ እስከ አለንበት ዘመን ድረስ የአምልኮቱ ዓይነት ይለያይ እንጂ ሁሉም በየወገኑ ባዕድ አምላክ ወይም ብዙዎች አማልክትን ያመልካል። ይህም ሁሉ የሚያሳየው የአንድ እውነተኛ አምላክ መኖርን ነው። እግዚአብሔር ባይኖር ሰው ይህን የአምልኮት ጠባይ ከየት ሊያገኝ ቻለ? (የሐዋ. 14፤11-16፣ 17፤26-29)። በቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እግዚአብሔር መኖር በሰፊው ከመነገሩም በላይ ስለ እርሱ የተሰጡ መግለጫዎች አሉ። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው።

<u>ቅድስና፤</u> እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፤ ክፉ ወይም ከርኩስ ነገር ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። እርሱ ራሱ «እኔ ቅዱስ እንደሆንሁ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» ሲል ተናግሮአል። (ዘሌዋ. 19፤2፣ 1ጴጥ. 1፤16)። ሁልጊዜ በመላእክት ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ እየተባለ ሲመሰገን ይኖራል (ኢሳ. 6፤3)

<u>ፍቅር፤</u> እግዚአብሔር ፍቅር በመሆኑ ፍጥረቱን ይወዳል መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ ለፍጥረቱ ይሰጣል። እግዚአብሔር ፍቅር መሆኑ በወንጌላዊው ዮሐንስ ወንጌልና መልእክታት ተደጋግሞ ተገልጦአል። (1ዮሐ. 4፤8) በኋላም ሰው መሆኑ ፍቅሩን ያመለክታል። (ዮሐ. 3፤16፣ ሮሜ 5፤5)።

<u>ጽድቅ፤</u> እግዚአብሔር በሁሉ እውነተኛ ነው። በእውነተኛነቱ ለሁሉ በትክክል ይፈርዳል (1ሳሙ. 2፤2፣ 2ጢሞ 4፤8)። ዮሐንስ በራእዩ 16፤7 «አዎ ጌታዬ ሁሉን የምትገዛ ፍርድህ እውነተኛና የሚገባ ነው» ይላል።

<u>ጥበብ፤</u> ፍጥረትንና የፍጥረቱን ሥነ ሥርዓት ክንውን ሰንመለከት የእግዚአብሔርን ፍጹም ጥበብ እንረዳለን። ነቢዩ ዳዊት እግዚአብሔር በጥበብ የሠራውን ሁሉ በማድነቅ እንዲህ ይላል። «አቤቱ ሥራህ እጅግ ብዙ ነው ሁሉን በጥበብህ አደረግህ» (መዝ. 103፤24)

ከአንድ እስከ አራት ከተመለከትናቸው የባሕርዩ መግለጫዎች የተለዩ ሌሎች የእግዚአብሔር የባሕርዩ መግለጫዎች አሉ።

<u>ሁሉን ቻይነት (ከሃሌ ኩሉ)፤</u> ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር ፈጽሞ የለም ሁሉን ማድረግ ይችላል። እግዚአብሔር ራሱ ለአብርሃም «ሁሉን ቻይ ነኝ» ብሎ ገልጦለታል። (ዘፍ. 17፤1። 18።14። ሉቃ.1፤37)

<u>ሁሉን ማወቅ፤</u> እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ከመሆኑ በፊት ያውቀዋል። ነገሮችን ሁሉ ከመታሰባቸውና ከመሠራታቸው በፊት ያውቃቸዋል። (መዝ 138፤2፣ ዮሐ. 2፤25)።

<u>ምሉዕነት፤</u> እግዚአብሔር በቦታና በጊዜ አይወሰንም በየትም ቦታ አለ ምንም እንኳን ስለ ልዕልናው በሰማይ እንደሚኖር ቢነገርም በሰማይ ብቻ አይወሰንም። ቅዱስ ዳዊት እንዲህ ይላል «ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለው? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ አለህ ወደ ሲኦልም ብወርድ በዚያ አለህ. . .» (መዝ. 138፤ 7-10፣ ኤር. 23፤23፣ ሠለስቱ ምእት ቅዳሴ)

<u>ዘለዓለማዊነት፤</u> እግዚአብሔር በዘመናት አይወሰንም። ከዘመን በፊት ነበረ፤ ዘመናትንም አሳልፎ ይኖራል (መዝ.89፤1-2) በጠቅላላ አነጋገር እግዚአብሔር መጀመሪያና መጨረሻ የለውም ራሱ መጀመሪያና መጨረሻ ነው ነእርሱ ዘንድ ለውጥ የለም። (ኢሳ. 44፤6፣ ያዕ. 1፣17)

www.ethiopianorthodox.org